# ሴት

## የፍቅር ግጥሞች እና እውነተኛ ታሪክ

ከ

ወርቅነህ ጉሉማ



*አስተያየታቹ ያስፈልገኛል*

*ለሃሳበና አስተያየት*

*ቴሌግራም @abilawww*

*ስልክ 0910901502*

# ሂወቴ

አንቺ ካለሽ ከጎኔ

አይዞ ብለሽ የደገፍሽኝ ያኔ

ያልሰጠሽኝ ነገር ምን አለ ለኔ፤

በችግር ጊዜ አይዞህ ያልሺኝ

አቅፈሽ ይዘሽ በደስታ የሳምሽኝ

አንቺን ርቦሽ እኔን ያጎረስሺኝ፤

እንዴትስ ሊረሳኝ.....

አረ ያንቺስ ፍቅር ለብቻው ነው

ቢለካስ ቢገመት የቱን ነው ሚያክለው፤

ለኔ ብለሽ በሳት መቃጠልሽ

ስትከራተቺ ውለሽ ማደርሽ፤

እኔን ከመውለድም ለዚአደረስሽ

ታድያ በየትኛው አፌ ላመስግንሽ ?

አንቺኮ ሂወት ወርቅ አልማዜም ነሽ ፡፡

# እንዴት ላረጋግጥልሽ

**‹‹‹እውነተኛ ታሪክ›››**

በፍቅር ሲቃ ስትሰቃዪ

እንደዛ በይ ስልሽ እንዲ በዪ፤

ላንቺ ፍቅር ደስታን ስሻ

ያንቺን ፍቅር ሳሰምር ሆኜ ሆደ ባሻ፤

ስለምውድሽ እኮ ነው ላንቺ ደስታ ብዬ

የኔን ፍቅር ልቤን መሻት ገድዬ፤

አንቺን ደስ ብሎሽ ብለሽ ምክርህ ሰርቷል

የኔስ ፍቅር ባንተ ምክር ተሳክቷል፤

በሆዴ ሳለቅስ ያከተመ መስሎኝ

እኔ ግን ስጠብቅሽ እስካሁን አለሁኝ፤

ታድያ ምን ዋጋ ያ ሁሉ ቀረ

እሱም አንቺን ትቶ ሌላ አፈቀረ።

እንዳለፈው ፍቅር ምኅዳሽመስሎሽ

ላንቺ ያለኝ ፍቅር ጊዜአዊ መሰለሽ።

ባላፈቅርሽኑሮ........

ባሎድሽ ኑሮ ለምን ረዳሻለው

ላንቺ ደስታ ብዬ ምክሬን ለግሻለው

ባታምኚም አንቺ እኔ ወድሻለው።

# ትዝታ

አጠገቤ እያለሽ ሳላስቀይምሽ በፊት

ስወድሽ ስልሽ ልብሽ ደስ እያላት

እኔም ወድሀለው ስትይ የልቤ ሀሴት፤

አጠገቤ እያለሽ ሳላስቀይምሽ በፊት

ብዙ ፍቅር ነበረን አብረን የዋልን ለት።

አሁን ግን በቃ ያሁሉ የት አለ

ያንቺ ልብ የኔን የኔ ያንቺን ያለ፤

አሁንማ..........

አይኔ ይቅርታሽን ሁሌ እየማተረ

በትዝታሽ መአበል ልቤ ፈዞ ቀረ፤

አይኔ አነባ ፍቅርሽን ማተረ

የልቤ እርካብ ጠፋ ተሰባበረ፤

አይ ፍቅርሽ ያሳየኝ አበሳ

ትዝ ትዪኝ ጀመር ትዝታ ሲነሳ ።

# አየሁኝ

ከገላጣው አስፋልት ሰውከሚበዛበት

ሰው ለስራው ሚወጣ ሚገባበት።

ከጥጉ ተቀምጦ አየው እጁን ሲዘረጋ

የሰው ፊት ሲገርፈው መሽቶ እየነጋ፤

ለቁራሽ ዳቦ የሰው ፊት አሳየው

በመብርሃን ብሎ ሲለምን ሳየው፤

ፈጣሪስ እስከመቼ እንዲ የሚአኖረው ?

ርቆ ካጠገቡ አለች ሴት ልጅ ታቅፋ ላያት

ቀን በ ጸሀይ ማታ ብርዱ ሊያሰቃያት፤

ሆዱ ያልቻለ መጽዋት ሲሰጣት

ያልቻለ ክንፈሩን መጦ በስስት ሲያያት፤

የሷስ መከራ መች ይሆን በቃሽ የሚላት ?

ልጇስ በማን ጥፋት ጎዳና ተወለደ

ሜዳ ላይ ዳዴ መሄድን ለመደ፤

የሂወት ጉዳይ ሆኖ ሳይፈልግ ገብቶበት

ተፈጥሮ ከናቱ እሱአን ለመርዳት፤

ትንሽ አደግ ሲል ቦርሳ ነጥቆ ሲሮጥ

በፖሊስ ላለመያዝ በጎዳና ሊያመልጥ፤

የሱ ሂወት ሆኖ ግድ የገባበት

በቃ ሂወት እንደዚ ናት።

# ሳስብሽ እጎዳለው

ፍቅራችን  ነበር ካጥናፍ እስከ አጥናፍ

ጊዜያት አልፈዋል ገዴም ሳንኳረፍ።

ነበር........

በማህላችን ርቀት አልነበረም

እውር  ነን ሌላም አናይም፤

ጆሮም የለን ፣ሌላም አንሰማም

እጆቻችን ሌላም አያቅፉም፣

እግራችንም አይርቅም።

ታድያ......

ታድያ ውዴ ምነው ተቀየርሽ

የታል ያ እኔን ያለው ልብሽ፤

ያቀፈኝ ክንድሽ ፣ያልራቁኝ እግሮችሽ

ሌላ ማያየው አይንሽ፣ ሀሜት ማይሰማው ጆሮሽ።

ምነው....?

ለኔ ጊዜ ያጣሽው ፣አይንህን ላፈር ያልሽው ?

ተለያይተን ስንቀር ይሀው ጎኔን በረደው

ከንፈሬ  ተራቡ ከንፈርሽ ናፈቀው፤

መለየትሽን ሳስብ ውዴ እጎዳብሻለው

መንገድሽ ይቃና እኔም ይሄው ሄጃለው።

# ህልም

ውዴ ሀሳብም ሀሳብ ነው ምሽትም ምሽት

ካልጋይ ብተኛ አንቺኑ ለማየት፤

ብገላበጥ ብገላበጥ ለሊቱ ማያልቀው

ከንፈርሽእኮ ነው ደሜን የሚያሞቀው።

አንቺ ከሌለሽ ህልምም እርም ነው

ከጎኔ ስተኚ ሌሊቱ ሚነጉደው፤

ውድ በህልሜ ነው....?

በድቅድቅ ጨለማ አንቺን የማስበው

ውዴ ማር ስትዪኝ በጆሮዬ ሚያቃጨለው፤

እውነት ጠርተሺኝ ነው ?

ካይኔ ፊት ለፊት ውልብ ምትዪው

ክንዴን ተንተርሰሽ ጎኔን ምትዳብሽው፤

እውን ይሁን ይሄ.. አልንቃ ካለሁበት

ጊዜያት ይለፉ ይቆጠሩ አመታት፣

ያንቺ መኖር ለኔ እንዲሆነኝ ብርታት።

# መልሺ

አንቺ የኔ ንግስት ነይ ልቤ ላይ ንገሽ

እንደፈለክሽ ሁኚ እዘዢ  እንደ ልብሽ

አንቺ ብጠዪቂኝ ምን አለ የማልሆንልሽ፤

ላንቺ ማሎነውን ሁሉ ሆኜልሻለው

የሂወትን ጣእም አቅምሼሻለው፤

ላንቺ ያለኝን ፍቅር አሳየቼሻለው

እንደ ንጉስ ሆኜ ንግስቴን ጠብቄአለው፤

እኔ ግን ባላዝሽም ጥያቄ ልጠይቅሽ

ለምታዢበት ስፍራ ከምር ቦታ አለሽ ?

ስለፍቅር ብለሽ አንድም ሳትዋሺ

ዕውነተኛ ፍቅርን ከሆነ ምትሺ፤

የጠየኩሽን ጥያቄን መልሱን መልሺ ?

# ሰላምና ጥል

**‹‹‹እውነተኛ ታሪክ›››**

ሰላም ነን ስንል እንጣላለን፣

ተጣላን ሲባል እንታረቃለን

አብረን ሆነን ተለያየን፣

ተለያይተን እንተሰሰባለን

እኔ ያንቺ አንቺም የኔ ሆነሽ

ካንቺ ርቄ አንቺም ከኔ ርቀሽ፤

ብንጣላም አልተለያየንም

ብንለያይም አልተጣላንም።

እንማስብሽ ከቀን እስከማታ

እመጣብሽ ይሆናል በሃሳብሽ ውልብታ፤

ሳፈቅርሽ ምቶጂኝ

ስወድሽ ምታፈቅሪኝ፤

ሰላምና ጥል መለየት አቅቶን

እንዲ የሚያደርገን የውነት ፍቅር ይሆን ?

# ፍቅር ማለት ለኔ

ፍቅር ማልት ለኔ እራስን መርሳት ነው

ለወደዱት መኖር እራስን መስጠት ነው፡፡

ላንቺ ደስታ ብዬ ካንቺርቄአለው

ሂወቴን ትቼ ራሴን ጎድቻለው፤

እንዳትጎጂ ብዬ እንደማሎድሽ አስመስያለው

ምክንያቱም ወድሻለው፡፡

በርግጥ……

ባፌ ወድሻለው ከማለት ውጪ ምንም አላረኩም

እስከመጨረሻው ድረስ ለፍቅር አልሞትኩም፡፡

ፍቅር በትግል ከሆነ የምር አሎድሽም

ደሞ ከሆነ ማሎድሽ፤

ለምን ፎቶሽን ሳይ ደስታ ይሰማኛል

ሳቅና ፍገግታሽ ባይኔ ይታየኛል፤

ስላንቺ ሳስብ ሰውነቴ ይነዝረኛል

አሁንስ አልቻልኩም በቃ ይበቃኛል፡፡

# አትጣዪኝ

**‹‹‹እውነተኛ ታሪክ›››**

ስላንቺ ስጽፍ ውዬ አድሬያለው

አንቺን ሳስብ ዘፈን ዘፍኜያለው

አንቺ ያለሺው ግጥሜ ውስጥነው።

የምጽፈው ግጥም አንቺን ላይሰጠኝ

ያጽናናኝ ጀመረ ካንቺ እያራቀኝ፤

ምክንያቱም……

ዘፈንኩኝ ስላንቺ እንጂ መቼ አሰማውሽ

ጻፍኩኝ ስላንቺ እንጂ መቼ አስነበብኩሽ፤

ስላንቺ ስጽፍ አይኔም አልቅሱአል

ልቤም ያሰበውን ጽፎት ጨርሷል፤

ሀሳቤም ተኖ ፣ ካሌም ተጎድቷል

ስላንቺ ሲያስብ እራሱን ትቷል፤

አሁንስ በቃኝ ብዙ ተሸወድኩ

መገኘት አልፈልግም ቆሜ እያበድኩ፤

ያበደው እኔነቴ አንቺን እየተመኘ

በፍቅርሽ ታርሶ ተስፋካላገኘ

አብዶ ይቀራል ሁሌ እንደተመኘ።

ስለዚ ፍቅሬን መውደዴን ከተረዳሽ

እኔም በተስፋ ቆሜ ከምጠብቅሽ

እባክሽ ነይና አለውልህ በዪኝ

ብቻዬን ለተስፋ ጥለሽ አትጣዪኝ ፡፡

# ስለ ፍቅር

ዘፋኞች  ዘፈኑት፣ ጠቢቦች ተጠበቡት
ታሪክን ሰሩበት፣ ልብወለድ ጻፉበት
ቅኔዎች ተቀኙለት፣ ስለ ሃይሉ መሰከሩለት
ስለፍቅር ብለው ብዙ ተረኩለት
ጌታችን በምረቱ ለፍቅር የሞተለት
በቸርነቱ ትምርት ያስተማረበት
መስቀል ተሸክሞ የተንገላታበት
የፍቅርን ትምህርት ሞቶ ያሳየበት።

ደሞም በፍቅር ተነግዷል
ስንቶች ሸጠው አትርፈውበታል።

እሷም ክብሯን ሸጣ ኑሮ ሞልቶላት
ተደስታ ስትኖር ፍቅር ሳይኖራት
ሂወቷ ጨልሞ ብዙ ስትዋትት
እሷም ታስራ ቀረች ባምሮ ፀፀት።

አንተስ ቢሆን ለፍተህ ባገኘኸው ሀብት
ሴትን ለመማረክ ብትጠቀምበት
የታል ያንተስ ደስተኛ ሒወት ?

# አይኔ

**‹‹‹እውነተኛ ታሪክ›››**

ሀ ተብሎ ትምርት ሲጀመር

እኔን የጀመረኝ ያይን ፍቅር ነበር

ያን ለት በተቀመጥኩበት ቦታ

አይኔ እያማተረ ሲጫወት ጨዋታ

በፍቅር ተያዘ ወደቀ ባንዳፍታ

ወይ አላናገረሽ ትንፋሽ አላወጣ

ሁሌ ያይሽ ጀመር ጠዋት እየመጣ

ከፀጉርሽ መርዘም፣ ከቁመት ማጠር

ከዳሌሽ ውበት፣ ከጡትሽ ማማር

ከመልክሽ ደምግባት ሁሉ ሲደመር

አጀብ ያስብላል ያንቺ አፈጣጠር

ሰርቆ ሲያይሽ በጥርስሽ ፈገግታ

ሳስብሽ ስውል ከጧት እስከ ማታ

ምንም መናገር ባልችል ልሳኔ ቢገታ

አይኔ ይናገራል የልቤን ትርታ ።

## የቱ ነው

ላንቺ ሚሆን ይት አለ?

ካንቺውጋር መኖርን የታደለ?

አንቺን ለማስደሰት ምለው ተገዝተው

ውብ ገላሽን ለማቀፍ ታቦታትን ጠርተው

አንቺ ምትፈልጊውን ሁሉ ቢያደርጉልሽ

ግን ከልብ የቱ ነው ከልብ የሚወድሽ ?

እኔን የገረመኝ........

ምንድን ነው ችኮላ?

ለማቀፍ ውብ ገላ፣

ለስሜት መሯሯጥ

እረክቶ ለመሮጥ፣

ጉዳትን ሳያስቡ

እራስን እየካቡ፣

አደረኩ ለማለት

ለጓደኛ ለማውራት፣

እሷ ሴት ናት

እንክብካቤ ሚያስፈልጋት

ፍቅርን ምትሻ ሁሉ ሚገባት።

# ካለህበት

ብጠራህ ብጠራህ አንተስ አትሰማኝ

ለፃፍኩልህ ሰው ላንተው ይድረስልኝ

አብረን ሳለን ያሳለፍነው ጊዜ

የሌለህ ወቅት ሲሰማኝ ትካዜ

አሁን ለምን አትመጣም በጣሙን ናፈከኝ

እኔ ካንተ ውጪ እንዴት ሆናለውኝ

የውነት ፍቅሬ ካለህበት ይድረስልኝ

በመንፈስም ሆነ በውሃ ይምጣልህ

ይድረስልኝ ላንተ በጣም እንደምወድህ።

# ስቶ ነሳኝ

አየሁሽ አየሽኝ ወደድኩሽ ወደድሽኝ

ስልክሽን ጠየኩኝ አንቺም ሰጠሽኝ

ስናወራ ቀናትም ሄደው ወራትም አለፉ

ያሁሉ ጊዜ ሰአትና ሰከንድ እንደቀልድ ከነፉ

መረሳሳት መጣ ሳንገናኝ ስንቀር

የኔ ፍላጎት ሲኖር ያንቺ ሳይኖር ሲቀር

መገናኘት እንዳለ መለያየት  ቢኖርም

ደሞ ተለያይተን በዛው  አልቀረንም

ጊኤ እኔና አንቺን ምንም ብትለያየን

እሷም አቅም አታ ድጋሚ ተያየን

ድጋሜ አየሁሽ በጣም ደስ አለኝ

ፍቅርሽ ተቀሰቀሰ አገረሸብኝ፡፡

ሌላ ሴት ላላይ ልቤ ይዞ መሀላ

ስትነግሪኝ ደነገጥኩ መሆንሽ የሌላ

አዬ ጊዜ ሰቶ ሲነሳ አሳይቶ ሲነፍግ

ችሎ ይኖራል እንጂ ታድያ ምን ሊደረግ

የሰጠንን ሰቶ የነሳውን ነስቶ ብር ብሎ ሲጠፋ

አንቺን ማስታወሱ ሆነ የኔ ቀሪ ተስፋ፡፡

# እንደመስቀል ወፍ

ጠፍተሽ ጠፍተሽ ትመጪና

የናፈቀሽ አይኔን በጩረፍታ ታይና

ደሞ ትጠፊያለሽ ማንም እንዳያይሽ

ድምጽሽ እንዳይሰማ እንዳይታውቅ መሄጃሽ

ደሞ በጫወታ ሰበብ እየመጣሽ

ጉንጬን እንዳልሳምሽ ደግመሽ ደጋግመሽ

በፈገግታሽ መሃል በሳቅሽ አስረሺኝ

የቁም ሰመመን ውስጥ ከተሺኝ

አብደሽ ልታሳብጂኝ ከጫፍ አደረሺኝ

እህቴ ነች ጓደኛዬ ብዬ....

ከራሴ ጋር ስታገል ከህሊናዬ

ታድያ ይሄ ሁሉ ለምን ለብቻዬ።

## ውሽታም

ከኔጋር ለመሆን ምለሽ ተገዝተሽ

አብረን ሆነን ፍቅር ካለቀብሽ፤

ያለሽን ትቶ ልብሽ ሌላ ካስከጀለሽ

አዎ እልሻለው ውሽታም ነሽ።

አንድላይ ስኖን ስለፍቅር አውርተሽ

ብትነግሪኝ መሆኔ የፍቅር ምርጫሽ፤

ከወራት በኋላ ፍቅርሽ ካለቀብሽ

ድጋሜ ልንገርሽ አዎ ውሽታም ነሽ፤

በቃልሽ ከኖርሽ ፍቅርሽን አስበሽ

በፍቅር ምኖርን ከሆነ የመረጥሽ

አሁን አልሰድብሽም ከልቤ ልመርቅሽ

ለ ፍቅር የታመንሽ

ፍቅር ማለት አንቺ ነሽ

አንተን ደሞ ልስደብክ

እሷ ተሰድባ ለምን አንተስ ይቅርብክ

ሴትን ለመማርክ መግዛት በማሰብክ፤

አንድን ሴት ወደክ ሌላ መደበልክ

ከዚችኛዋም ሌላ መጨመርክ፤

ከምር ልንገርክ ስድብስ አነሰብክ

ደስ ካለኝ ደግሜ ሰድብካለው፤

ከምርቃቴም በፊት አከናንብካለው

አንዷን ለፍቅር ካሰብክ ሌላዋን ለ ቅምጥ ካሰብካት

በሰጠችህ ፍቅር ሙድ ከያዝክባት፣

ሚገባትን ፍቅር ና እንክብካቤ ካላረክላት

አንድ ጊዜ ራስህን ዞር ብለክ እየው

ያለዛ  መጥቼ ሰድብካለው

እስቲ ደሞ እናንተ ስሙኝ

ተሳደበ ብላቹ ከምታሙኝ፤

ስሙኝ እናንተን ራሱ ልስደባቹ

እሱም እሷን ሲደፍር ቆማቹ ካያቹ

እሷም ወንድ ስትቀይር ዝም ብላቹ ካለፋቹ

እኔ ቆጥረዋለው ሀገር እንደከዳቹ።

## ዘመናዊነት

ቀሚስ ተትቷል

በሱሪ ተተክቷል፤

ዘመናዊነት በሰው ላይ ነግሷል

ሱሪዋ ዳሌዋን አጣብቋል፤

ቲሸርቷ ከፍ ብሎ እምብርቷ ይታያል

ጡቷ ከቦታው ወቶ እዩኝ  እዩኝ ይላል፤

የአዳም ዘርን ያሳስታል፡፡

በርግጥ እኔም ስቻለው

ከ ውቧ ኮረዳ እኔም አመዝሬያለው

ውበቷ አይጣል ነው ለሚያያት ሰው

በመልኳ ተማርከናል በሚያብረቀርቀው

ከተቀደደቀው ሱሪዋ በሚታይ ገላዋ

ብለን ስንቃኝ እየተባለ ሽንጥ ና ዳሌዋ

እኔም እላለው ከዋላ ከዋላዋ....

# አይምሰልሽ

ክብርም ካልገባሽ ፍቅርንም ካልፈለክሽ

ወደሌላ መሄድን መሮጥን ከመረጥሽ፤

ያለሽን አስንቆ ሌላ ካስከጀለሽ

አልይዝሽም ሂጂ ፍቅርን እዚያው ከገኘሽ፤

እኔም እልሻልው በሄድሽበት ይቅናሽ

ግን ግን........

በሄድሽበት ቦታ በሄድሽበት መንገድ

እንደኔ ባይሆንልሽ የመረጥሽው ወንድ፤

አስታውሺ ትተሽ የሄድሺውን

እረግጠሽ ስቴጂ ዞር ብለሽ ያላየሺውን

ደሞ......

ወደኔ ድጋሜ ለመምጣት ካሰብሽ

አይምሰልሽ ደስ ብሎኝ ምቀበልሽ

ፍቅር ማለት ሄዶ መምጣት አይምሰልሽ

## ጠብታ እምባዎች

ከመከፋት ጀርባ የሚንጎራደዱ

ልውጣ ልውጣ ብለው አይንን የሚያነዱ፤

አሉ ጠብታእንባዎች ሲበዙ ሚወርዱ

ከ አይን ተነስተው አስከአንገት የሚወርዱ፤

የሰውን ስሜት ጉዳትን እጂግ የሚያስረዱ

የሚያነቡ የሚወርዱ ዕምባዎች

ምስክር ሚሆኑ ለተጎዱ ሰዎች፤

የራስን ሂወትና በደል ሚተርኩ

ለሰዎች ተናገረው ጨርሰው ማይረኩ

ጉዳት ደርሶባቸው ታምቀው ለተያዙት

ይናገራሉ እነሱ ካይን የሚወጡት።

## የተቀጠፈችው አበባ

**‹‹‹እውነተኛ ታሪክ›››**

ብዙ  ይሰማል

ያልተሰሙ ብዙ ታሪኮች አሉ

ያልተነገሩ ብዙ እውነቶች አሉ

ያልተነበቡ ተጽፈው የማያልቁ

ተረት ተረት...............የውነት የውነት

ደስተኛ የምትመስል ውስጧ የተጎዳ

ውጪዋ የሚያምር ውስጧ ጨምዳዳ

ጥርሷ የሚስቅ ውስጧ ብዙ ጉድ ያለው

በሂወቷ ደስተኛ ለመሆን ምትሞክረው

የእውነት.....የእውነት

እኔስ ይገርመኛል የሰው ከንቱነት

አባት ለልጁ ክፉ የሆነበት

ፍርድ ያልተሰጠው ያልተወሰነበት

ምንም ያልመሰለው ያልተሰማው ጸጸት

ባባት ስሜታዊነት ልጇ የተጎዳበት

የእውነት.......የእውነት

ልጂት ምን ትተንፍስ ምንስ ቃል ታውጣ

ለመናገር ሚከብድ ቃል የማያሰጣ

ከወላጅ አባቷ ለደረሰባት በደል

ፍርድ የማትፈልግ ፈጣሪ ዋጋውን ይክፈል

የእውነት........የእውነት

በጨቅላ እድሜዋ ገላዋ ለረከሰው

ለደረሰባት በደል ለፈጣሪ የሰጠችው

ቢያስፈራራት አባቷ ከንደበቷ እንዳይወጣ

ችላ ለኖረችው የገላዋን መርከስ በደሏን ውጣ

እኔ ልተንፍስ ቃላቶችን ላውጣ

# እመኚኝ

አካሌ ሆዴ፣ ፍቅሬ እመቤቴ

ብትለኝ አንጀቴ፣ አንቺ ነሽ ጉበቴ፤

እወድሻለው  ካላንቺ ሰው የለም ብትለኝ

ፍቅሬ ነሽ ማረጌ እያልክ ብታሞካሸኝ፤

እባክህ ውዴ እመኚኝ አትበለኝ

እኔ

እኔ ግን እልሻለው ከልብሽ አመኚኝ

ለፍቅርሽ  ስታመን አትጠርጠሪኝ፤

ፍቅርኮ ዕምነት ነው አደል ጥርጣሬ

መዋሸት ማስመሰል የለውምኮ ፍሬ፤

ደግሜ ልበልሽ ከልብሽ አመኚኝ

ጥርጣሬሽ ቅጥ አልፎ እኔን ከምታጪኝ።

# የሰው ነሽ

አብረን ውለናል ይህንን አውቃለው

እቅፌ ውስጥ ሆነሽ እጅሽን ይዣለው፤

መን ገድ ላይ ሆነን ስንራመድ ላዩን

እጅሽ እጄላይ ሆኖ ፍቅረኛሞች መስለን፤

በልቤ ጸልያለው አንድ ላይ እንዲያረገን፡፡

አልዋሽም ብያለው ከባልሽ ያጣላሽ

ከእቅፌ ወደስጥ ገብተሽ በዚያው ዕንዲያስቀርሽ

እና ማልዋሽሽ አንቺ ሳታውቂው

ካንገትሽ ላይ ካለው መአዛ ትንሽ ወስጄብሻለው

ከ ልቤ ና ከ ልብሴ ከታተመው ሽቶሽ

በ ቀን ብቻ ሳይሆን ተኝቼ ማልምሽ

በጆቼ ክንዶች ከሰረኩሽ መዳኒት

የልቤን ሀሣብ ፍቅሬን ማክምበት

ለካ ተሽድኩ ጭራሹን ባሰበት

ባምሮዬ ትዝታ ባፍንጫዬ እየማግኩት

የባስ ታምሜያለው መዳኒት ነው ባልኩት

ሽቶሽግርማ አለው ..አለው የደስደስ

ልብ ውስጥ ገብቶ መንፈስን የሚያድስ

አልረተሳውም ውዴ አዎ የሰው ነሽ

አልልም ደግሜ ከሱጋ ያጣላሽ

ክፉ ሆኜ አደለም እውነት ነው ስለምወድሽ

አልረሳሽም ሁሌ በማሸተው ሽቶሽ።

## አምጣት

ስሜቱ ምን እንደሆነ አላውቅም

ከዚ በፊት ተሰምቶኝ አያውቅም

እጄ በፍርሃት ልቤ በመንቀጥቀጥ

አካሌ ደርቆ ቆማለው እንደ ሃውልት

ታድያ

ለዚ ሁሉ ምክንያቱ አንቺው ነሽ

ስቴጂ ስመጪ ባይኔ ምከተልሽ፤

ከተቀመጥኩበት ድንጋይ ሰዎች ሚተርቡኝ

ዱርዬ ነው ስራ አጥ ባይናቸው ሚገላምጡኝ፤

አንቺ ነይ እንጂ ገዴለም ይስደቡኝ

ታድያ......

ለዚ ሁሉ ምክንያቱ አንቺ ነሽ

አንቺ ያልመጣሽ እለት ለምን ይከፋኛል

ሃሳቤ ከራሴ ጋር ይነታረከኛል

እሷን አምጣልኝ ፈልጋት ይለኛል

ደሞ እነሳለው አንቺኑ ልፈልግሽ

በሃሳቤ እየገመትኩ ምን እንደገጠመሽ

ታድያ አንም....

ለዚ ሁሉ ምክንያቱ አንቺ ነሽ

ስፈልግሽ ምውለው ይሄው በመቅረትሽ።

## ስጠብቅሽ ከረምኩ

አንቺ መተሽ ከሄድሽ በዋላ

ክረምት መጣ ተመልሶም ሄደ

ፀኃይ ጠፍታ ጨለማም ቀንን ወርሷል

ጨለማም በተራው ለ ፀኃይ ቦታ ለቋል

ይሄሑሉ ሲሆን እኔ ግን እዛው ነኝ

ስቴጂ እያየው መናገር ያቃተኝ።

## ንፁ ልብ

የታለ ?

ክፋት የማይወጣው ደስተኛ የሆነ

የፈጣሪ መቅደስ በሰላም የታጠነ

የታለ ?

ጭንቀትን የማያውቅ የተረጋጋ ሂወት

ባህሪው መልካም የማያውቅ ስህተት

የታለ ?

እንደ ልጅ ንፁ ልብ የታደለ

ደስተኛ ሆኖ መኖር የከጀለ

በእቃቃ ጨዋታ ሱዚ እስከ መዝለል

በድርብርቦሽ ጨዋታ ዛፍ እስከመንጠልጠል፤

በአያ ጂቦ እሩጫ ተይዞ እስከ መዘንጠል

በሌባና ፖሊስ ሩጫ ታስሮ የታሰረ፤

ልጅ ለመፈለግ መተናል ብሎ የዘመረ

ኦሊ ደስቶ ፈንገር ጣቶች ተቆጥሮ፤

ሰኞ ና ማክሰኞ በልዩና አንዳይነት ዕጅ ተወርውሮ

እንደዛ ነበር ድሮ

ሃሳብ የሌለበት የ ንፁ አለም ኑሮ።

## መብራት ሲጠፋ

ቀኑ ጨልሞ መብራት ሲጠፋ

አልጋ ላይ ሆነን በ ፍቅር ስንላፋ፤

ገላሽ ይሞቃል በቀን ብቻ አደለም ሌሊትም ይደምቃል

ቀን የሰበሰበውን ፀሀይ ማታላይ ይለቃል

ብቻ ሰውነትሽ ይሞቃል

አንቺን ያቅፍኩ እለት ቀለጥኩ እንደብረት

ከንፈሬን ስትስሚኝ ጠፋኝ ያለሁበት

.

.

.

.

.

.

## ምንድን ነው መዋለድ

ምንድን ነው መወለድ?

ምንድን ነው መዛመድ?

ለተቸገረ ቶሎ ካልደረሱ

ሚፈስን ውሃ ደርሰው ካላፈሱ

ምንድነው መዋለድ?

ምንድነው መዛመድ?

ወገን ሲያዝን እሩቅ ሆነው ቢያደምጡ

ካለፈ በዋላ ከንፈር ቢማጣጡ

መመለስ አይችሉ ምንም ቢራወጡ

የሞተን ከመቃብር አንስተው አያወጡ

ምንድነው መዋለድ?

ምንድነው መዛመድ ?

## የህልም አለም ኗሪ

ሳስብሽ እኖራለው በሀሳብ አሻግሬ

ከሰዎች መሐል  ትኖሪያለሽ በሚል ተስፋ ጥርጣሬ፤

አሻግሬ አያለው አይኔን አማትሬ

ማታ ሳስብሽ አድራለው ትመጫለሽ ብዬ በሕልሜ

ብርታት ጥንካሬ አንቺው ነሽ ድካሜ

ከተዘጉ አይኖቼ አንቺን አንቺን የማይሽ

ሳትኖሪ ካጠገቤ ብህልሜ ምስልሽ፤

ከጎኔ ያለሽ ምትመስዪኝ አቅፈሺኝ የተኛሽ

ጡቶችሽ የሚታየው ከነጩ ቢጃማሽ፤

ፀጉርሽ የሚለሰልስ ክንዴን የተንተራሽ

ቀስ ብዬ ብጠጋ ከንፈርሽን ልስምሽ፤

ነቃው

ለካ ውዴ ስነቃ አጠገቤ ጭራሹን  የለሽም

በህልም አለም እንጂ ባካል አላየውሽም።

**ጊዜ**

አንቺኮ ልዩ ነሽ ጊዜም አልፈጀብሽ

ቤትሽን ሰርተሽ ልቤ ላይ ካረፍሽ

እንዴት ልንገርሽ ወድያው መውደዴን

ፍቅሬን ልንገርሽ ልተንፍሰው የግዴን፤

አታምኚኝም ብዬ መስሎሽ የቀልዴን

ጊዜ መቁጠሩ ለ ፍቅር አይሰራም

ከልብ ካልሆነ አምታት ቢቆጠሩም መለያየት አይቀርም

ስለሂህ ፍቅሬ

ጊዜ አይርዘም ፍቅሬን ልግለፅልሽ

ካውኩሽ ጀምሮ ነው ልቤ የወደደሽ።

## ሊስትሮ

ሸራ ነው፣ ቆዳ ክሬም ነው ቀለም

ስራ ሳይንቅ ሚሰራ ስንት አለ ባለም።

ሰርቆ ማደግ ማይፈልግ ከቶ የማይሻ

ታግሎ የሚኖር ዕስከ ሂወት መጨረሻ፤

ከስር አጎንብሶ ቆሻሻን ሚያፀዳ

ከወገን ማይቆጥሩት ሚያዩት እንደባዳ፤

አትንኩኝ ባይ  ሰዎች የሚፀየፉት

ከስራ ትንሽ ከሰው የሚያቀሉት፤

ለተቀደደ ወስፌ የሚታገል ከክር

ያኮራል እንጂ ከቶም አያሳፍር።

## ሒወት አጣፍጥም

ሽንኩርት ተጨምሮ በዘይት ሲቁላላ

በፍቅራችን መሃል የማንሰማ ሌላ፤

በርበሬ ተጨምሮ፣ ሽንኩርቱ ሲታሽ

መለያቱን አናስበውም ጭራሽ ፤

ውሃ ተጨምሮ ፣ድስቱ ሲከደን

አንቺን ባጣ እሆናለው በድን፤

ሽሮው ተጨምሮ፣ ሲማሰል እንዳይጓጉል

አንቺን አጥቼ ሳልሆንብሽ አጉል፤

ጨው ሲጨመር ፣ሽሮው ቢጣፍትም

አንቺ የሌለሽበት ኑሮ ጭራሽ አይጣፍጥም።

## ገነት

አንቺ የኔ አበባ የበቀልሽ በገነት

የልቤን ብርሃን  ታግለሽ ያወጣሽ ከአለት

አሻግሬ ባይሽ ምማረክ ባንቺ ውበት።

እኔ ያንቺ አፍቃሪ

እጄን ብዘረጋ በቅፌ ማልይዝሽ

ከኔ ራቅ አርጎ በገት ያኖረሽ።

እኔ ያንቺ አፍቃሪ

ቤቴን ቀልሼ በሃሳብ ካንቺጋራ ኗሪ፤

በጥርስሽ አጥር የሆነኩኝ ታሳሪ

በውበት ማበል የተንገላታው አፍቃሪ።

ባንቺ ፍቅር የመነመነ ገላ

ላንቺ ስኳትን አፈር የምበላ፤

ሃሳብና ጭንቀት ውስጤ የሚብላላ

አንቺ የኔ እንጂ አቱኚ የሌላ።

## ትዝታሽ ይግደለኝ

ውዴ…ተዋዶ መኖር ቢኖርም

በፍቅር መሃል መጣላት አይቀርም፤

አንቺ እና እኔ ብዙ ብንራራቅም

ያሳለፍነው ጊዜ ትዝታ አይተወንም፤

ምክንያቱም ነውና አንቺን ሚያስታውሰኝ

የጊዜ መንገድ ነው አንቺን ከኔ የሚያገናኝ፤

ኖራለው በትዝታ አንቺን ስለሚያሳየኝ

እውነት እልሻለው ትዝታሽ ይግደለኝ።